# የሳምንቱ መዝሙር

## ቸርነትህ ነው

ቸርነትህ ነው ያደርሰን እስከ ዛሬ
ቸርነትህ ነው የጠበቀን እስከ ዛሬ
ላመሰግንህ የኔ ጌታ በዝማሬ (2)

መከሊቴን ቀብሬ ባሳዝንህ
መብራቴንም ይዤ ባልጠብቅህ
በታላቅ ይቅርታ እንዳትረሳኝ
በፍቅርህ ጎብኝትህ ከሞት አውጣኝ
ከቤትህ እርቄ መች ጠገብኩኝ
በረሃብ በርዛት ተቸግርኩኝ
አምናለሁ አምላኬ እንድትምረኝ
ለይቅርታ መጣሁ ተቀበለኝ

**አዝ**

አንዳች እንደሌለኝ አውቀዋለሁ
ባንተ ቸርነት ግን እመካለሁ
የከበደው ሸከሜ ይቀለኛል
የቅርታህ ለባሪያህ ይደርሰኛል
በመቅደስህ ቆሜ ለመዘመር
ስራህን ለትውልድ ለመመሰከር
እኔ ማን ነኝ ብዬ አሰባለሁ
አመላክ ቸርነትህን አደንቃለሁ

**አዝ**

በሰው እጅ መመካት አቁሜያለሁ
እረዳቴ አንተ ነህ አውቄያለሁ
አንተ ከጠበቅከኝ በህይወቴ
ቅጥሬ አይደፈርም መድኃኒቴ
የኔን ስራ ተወው ተግባሬን
የመስቀሉን ነገር መርሳቴን
አዚሜን አንስተህ አነተን ልይህ
ኢየሱስ ክርስቶስ አምላኬ ነህ

## የፍቅር እናት

የፍቅር እናት የሰላም (x2)
ይናፍቀኛል ስምሽን ሳልጠራው ስቀር ማርያም

በህይወቴ ውስጥ በኑሮዬ
ቅደሚ ከፊት ከኃላዬ
ተደላደለ ልቤ
አንቺ አለሽና ካጠገቤ

ምኞቴም ይስመር ድብቅ ህልሜ
ልለፍ ወጀቡን ተቋቁሜ
የጌታዬ እናት ነሽ
ኃይልን ያድርጋል ፀሎትሽ

እንዴት እቀራለሁ ከመንገድ
አደራ እናቴ አሰቢኝ
ለሚያስጨንቀኝ ጠላት
ለምያሳድደኝ አትስጪኝ

ትላንትም ዛሬም አመስጋኝ ነኝ
የለም ለነገ የሚያስፈራኝ
ሜዳ ይሆናል ተራራው
ልጅሽ ስላለ ከኔ ጋራ

## ምስለ ሚካኤል

ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል ንኢ ሰናይትየ ማርያም (2x)
ንኢ (6x)  እመ አምላክ ንኢ ማርያም (2x)